የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን/Date: ታኅሣስ 14 2012

ቁጥር / Ref: ሳዒር/8.1/8/23/12

ለአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ
ለአ/አበባሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
ለደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
ለወልዲያ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
ለመቱ ዩኒቨርሲቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርሲቲ
ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርሲቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርሲቲ
ለወራቤ ዩኒቨርሲቲ
ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ
ለቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ
ለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ

**ጉዳዩ፡ <u>የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የምዘና ስርዓትና የሙያ መስክ (ፕሮግራም) ድልደላን ይመለከታል።</u>**

በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የጥናት ምክረ ሐሳብ መነሻ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በ2012 የትምህርት ዘመን እየተገበረ ከሚገኝባቸው የለዉጥ ሥራዎች መካከል አንዱ የመጀመሪያ ዓመት ኮርሶችን ማስጀመር መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም በዩኒቨርሲቲዎቻችን የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎችን በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት መሠረት እየተማሩ የሚገኙ በመሆኑ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ምዘና ሥርዓትና የተማሪዎቹ ወደየሙያ መስኮች (ፕሮግራሞች) የሚደለደሉበት አሰራር ላይ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ጋር 06/04/2012 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ በመመካከር ስምምነት ላይ ተደርሷል።

ስለሆነም የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ምዘና ሥርዓትና ተማሪዎቹ ወደየሙያ መስኮች (ፕሮግራሞች) የሚደለደሉበትን አሰራር የሚገልጽ <u>03</u> ገጽ መመሪያ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የላክን መሆኑ ታውቆ በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ሂሩት ወ/ማርያም ካሳ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለሚኒስትር ፅ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ ፅ/ቤት
- ለምርምርና አካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል
  <u>ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር</u>



Scanned by CamScanner

መግቢያ

ዩኒቨርሲቲዎቻችን የሚያፈሩዋቸው ምሩቃን ለሀገራችን የጋራ ልማትና ብልጽግና አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንደመሆናቸው መጠን የትምህርት ውጤታቸው በውድድር ዓለም ተነጻጻሪ እይታ እንዲኖረው ዘንድ ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምዘናና የሙያ መስክ (ፕሮግራም) ድልደላ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም የተማሪዎች ምዘና ስርዓት፣ የሙያ መስክ ድለደላና አወንታዊ ድጋፍ ሥርዓት ማዕከል አድርጎ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. የተማሪዎች ምዘናን በተመለከተ

   1.1. የምዘና ስርዓት

   ለመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ሁለት ጊዜ ከ10% የሚያዙ ተከታታይ ምዘናዎች የሚሰጡ ሲሆን የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናም የሚሰጥ ይሆናል። የሰሚስቴር ማጠቃለያ ፈተና <u>ሁሉን የኮርሱን ምዕራፎች</u> በተመጣጠነ መልኩ የሚዳስስ ሆኖ አጠቃላይ የኮርሱ ግቦች መሳካት አለመሳካታቸውን የሚመዝን መሆን አለበት። ይህም እንደሚከተለው የሚፈጸም ይሆናል።

   1.1.1. ተከታታይ ምዘና ........................................................20%

   1.1.2. የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተና (Mid-term Exam) ......................30%

   1.1.3. የሰሚስቴር ማጠቃለያ ፈተና (Final Exam) .........................50%

   1.2. የምዘና ውጤት ስኬልና ግሬድ (Total Earned Points, Scale and Grading)

   ተማሪዎች በተለያዩ ምዘናዎች ያስመዘገቡት ውጤት ድምር እና አቻ ውጤት ደረጃዎች በሚከተለው መልኩ የሚፈጸም ይሆናል።

| ተ.ቁ | Total Earned Points, Scale and Grading | | |
|---|---|---|---|
| 1. | 90 እና በላይ | A+ | 4.00 |
| 2. | 85 - 89.99 | A | 4.00 |
| 3. | 80 - 84.99 | A- | 3.75 |
| 4. | 75 - 79.99 | B+ | 3.5 |
| 5. | 70 - 74.99 | B | 3.00 |
| 6. | 65 - 69.99 | B- | 2.75 |
| 7. | 60 - 64.99 | C+ | 2.5 |
| 8. | 50 - 59.99 | C | 2.00 |
| 9. | 45 - 49.99 | C- | 1.75 |
| 10. | 40 - 44.99 | D | 1.00 |
| 11. | ከ40 በታች | F | 0.00 |



Scanned by CamScanner

2. የሙያ መስክ (የፕሮግራም) ድልደላን በተመለከተ

በተፈጥሮ ሳይንስና በማህበራዊ ሳይንስ መስኮች ተመድበዉ ትምህርታቸዉን በመከታተል ላይ የሚገኙ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በተወሰኑ የሙያ መስኮችና ፕሮግራሞች ማለትም ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ፣ ሜዲስን፣ ቬተሪኔሪ ሜዲስን፣ ፋርማሲ፣ ዴንታል ሜዲስን እና ህግ ላይ አንደኛ ሰሚስቴር እንዳጠናቀቁ የሚደለደሉ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ሁለተኛ ሰሚስቴር ሲያጠናቅቁ የሚደለደሉ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት በአንደኛ ስምስቴርም ሆነ በሁለተኛዉ ሰምስቴር ወደ ተለያዩ ሙያ መስኮችና ፕሮግራሞች የሚገቡ መደበኛ ተማሪዎች በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት የሚደለደሉ ይሆናል፡፡

አንደኛ ወይም ሁለተኛ ሰሚስቴር አጠናቀው የሚደለደሉትን በተመለከተ

- 2.1.የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት ...............................................20%
- 2.2.አንደኛዉ ሰሚስቴር አማካይ ዉጤት (GPA) ወይም የአንደኛና የሁለተኛ ሰሚስቴር አጠቃላይ አማካይ ዉጤት (CGPA)..................................................50%
- 2.3.ወደ ሙያ መስክ (ፕሮግራም) መግቢያ ፈተና .....................................30%

ወደ ሙያ መስክ (ፕሮግራም) መግቢያ ፈተና አጠቃላይ የተማሪውን ዝግጅት የሚመዝን ሆኖ በየዩኒቨርሲቲው በኮሌጅ ደረጃ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

3. በሙያ መስክ (በፕሮግራም) ድልደላ ወቅት አወንታዊ ድጋፍን በተመለከተ

3.1.ሴት ተማሪዎችን በተመለከተ

3.1.1. ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ሲወዳደሩ ተወዳድረው ባመጡት አጠቃላይ ነጥብ ላይ ተጨማሪ 5 (አምስት) ነጥብ ተሰጥቶአቸው የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

3.1.2. ከላይ 3.1.1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሴቶችን ተሳትፎ ለማበረታታት 20% ኮታ ይያዛል፡፡ ይህም ማለት፡-

- ከ80% ሁሉም ተማሪዎች (ወንድና ሴት) ከላይ በ2.1ና በ2.2 በተቀመጠዉ መሠረት ተወዳድረው የሚገቡ ይሆናል፡፡



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Scanned by CamScanner

- በተረጡ 20% ላይ ሴት ተማሪዎች ብቻ እርስ በርሳቸዉ ከላይ በ2.1ና 2.2 በተቀመጠዉ መስፈርት መሰረት የሚደለደሉ ይሆናል።

3.2. አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተወዳድረው ባመጡት አጠቃላይ ነጥብ ላይ ተጨማሪ 5 (አምስት) ነጥብ ተሰጥቶአቸው የሚወዳደሩ ይሆናል።

3.3. ከአዳጊ ክልል የመጡ ተማሪዎችን በተመለከተ

3.3.1. ከአዳጊ ክልል የመጡ ሴት ተማሪዎች ተወዳድረው ባመጡት አጠቃላይ ነጥብ ላይ ተጨማሪ 10 (አስር) ነጥብ ተሰጥቶአቸው የሚወዳደሩ ይሆናል።

3.3.2. ከአዳጊ ክልል የመጡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተወዳድረው ባመጡት አጠቃላይ ነጥብ ላይ ተጨማሪ 10 (አስር) ነጥብ ተሰጥቶአቸው የሚወዳደሩ ይሆናል።



Scanned by CamScanner